# አጼ ሚኒሊክ እና እቴጌ ጣይቱ  በደራሲ ተስፋዬ ገ/አብ አይን

ገላነው ክራር
Gelanew-kirar@hotmail.com

ተስፋዬ በሰሞኑ ጽሁፎቹ መነጋገሪያ ሆኗል። ጽሁፎቹን አነበብኩ። የተስፋዬን ጽሁፍ ሳያነብ የሚያልፍ ያለ አይመስለኝም። አሁን አሁን፣ በተለይም ካገር ከወጣ በኋላ የሚጽፋቸው አብዛኛዎቹ እውነትነት ቢኖርባቸውም፣ በርካታ ጉዳዮች ላይ በግልጽ መናገር ሳይችል እስካሁን አለ። በተረፈ ጽሁፎቹ በቋንቋ እየሰላ የሄደ ጸሃፊነቱን ይመሰክራሉ። ተስፋዬ የአጻጻፍ ስልቱ ውብ ነው። የግል ሃብቱ ነው። (አጫጭር አረፍተነገሮችን መጠቀሙ ከበአሉ ግርማ የተማረው የሚመስል ከመሆኑ በቀር [*ይህን ራሱም ተናግሯል ልበል?*])። እኔ "እንደወረደ" ነው የምለው የተስፋዬን ጽሁፍ። ዘይት ሲፈስ አይተህ ታውቅ ከሆነ እንዲያ ነው። ይወርድለታል። የአጻጻፍ ስልቱን እንደቀናሁበት አለሁ። በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ  ቁርጥራጭ ሃሳቦቹን እንዴት እንደሚያገናኛቸው (*ይህ ሁሉ አድናቆቴ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን እያሰብኩ ነው፣ ሁለተኛውን መጽሃፉን አላነበብኩም*) ... የተለያዩ ቁርጥራጭ ታሪኮችን እያንሰላሰልኩ እንደሱ የመጻፍ ችሎታ ቢኖረኝ፣ ስንት እና ስንት ታላላቅ ሃሳብ በውስጤ ያለኝ ይመስለኛል። ማንስ የሌለው አለ? "እያንዳንዱ ሰው በልቡ ውስጥ አንድ የሚጻፍ ታሪክ አለው" ያለው በዓሉ ግርማ ነበር? ..."የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን ባንድ ቀንና ሌት (24 ሰአት) ጨርሸዋለሁ።

አንዱ የሰሞኑ ጽሁፉ ("የአለማየሁ እህት") ሳሊምቢኒን ይጠቅሳል። የጳውሎስ ኞኞንም መጽሃፍ ከስሩ አስፍሯል--ከመጽሃፉ ርእስና ገጽ ጋር። በታሪክ-ቀመስ የፈጠራ ስራ ውስጥ፣ ደራሲ የባለታሪኮቹን ደግም ሆነ ክፉ ስራ የሚያይበት ማእዘን ትልቅ ሚና ይጫወታል። ታሪኩ እውነት ቢሆንም እንኳን *("እውነት አይደለም" ብለው እየሞገቱት ያሉ አሉ። እውነት አላቸው። ምክንያቱም በአንድ የታሪክ ጉዳይ ወይም በባለታሪክ ታሪክ ላይ በተለያዩ ጸሃፍት የተለያዩ ጽሁፎች ሊወጡ ይችላሉ። ታሪክ ደግሞ ለዚህ የተመቸ ይመስላል።)* በተለይም ኢትዮጵያ እንዲህ ፈታኝ በሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ባለችበት ወቅት፣ የአገሪቱን ግዛት እና ዳር ድንበር በማስከበር ረገድ አለማቀፍ እና ታላቅ ታሪክ ያላቸው መሪዎች ድክመት ላይ ማጠንጠኑ አልተመቸኝም። አለዚያ ግን መብቱ ነው። እልፍም ሲል ደራሲ ሲጽፍ እገሌን "ይመቸዋል?" "አይመቸውም?" ብሎ አይደለም። ይጽፋል። በቃ። ያሜሪካው ቢል ክሊንተንን ብቃት ባለው መሪነታቸው አሁን ድረስ ላሉ መሪዎች ምሳሌ ለመሆን ስለመቻላቸው የሚጽፉ ደራሲያን እና ጋዜጠኞች የመኖራቸውን ያህል፣ ከሞኒካ ሎዊንስኪ ጋር አላቸው የተባለውን የውስልትና ታሪክ እያነሱ አሁን ድረስ በካርቱን (cartoon) ስእሎች እና መሰል የፈጠራ ስራዎች እና ጽሁፎች የሚያብጠለጥሏቸው ሰዎች አሉ። ያንድን ታዋቂ ሰው ታሪክ ደራሲው የሚያይበት ማእዘን ነው የሚወስነው። የተስፋዬ ሁለቱም ጽሁፎች የሚኒሊክ እና የጣይቱ እንከኖች ላይ ያተኮሩ ናቸው።

ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን "ጴጥሮስ ያችን ሰአት" እና የሌሎቹንም የቀድሞ መሪዎች እውነተኛ ታሪክ በተውኔት መልክ ለመድረክ ሲጽፈው፣ ምናባዊ  የሆኑ ድርጊቶችን እና ሁነቶችን ጨምሮበታል። እንዲያም ሆኖ፣ ግን በገንቢ መልኩ ነው። ከብሄራዊ፣ ሞራላዊ እና "emotional" እሴቱ (value?) አኳያ ገንቢ ነው። ተስፋዬም ታሪክን መሰረት አድርጎ፣ ያልነበረበትን የዛሬ መቶ ምንትስ አመት የሆነውን ታሪክ "ምናባዊ" እይታውንም አክሎ ቢጽፍልን ስህተቱ አይታየኝም። ችግሩ ያለው በአፍራሽ መልኩ መጠቀሙ ነው። በቅርቡ ዳኛቸው ቢያድግልኝ፡-

> *"... የፖለቲካውን አቅጣጫ የሚቀርጸው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ትስስር ነው። ይህንን በማጎልበት፣ ከድክመታችን ይልቅ ጥንካሬያችንን የሚገልጹ፣ ከተሸናፊነት ይልቅ አሸናፊነትን የሚያበስሩ ከክስና እርግማን ይልቅ ሽልማትና ምርቃትን የሚዘክሩ ነገሮችን ብንሰራ .....  እንደተፈለገው ኢትዮጵያ መሞት ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ኢትዮጵያ እንድትወደስ ማድረግ ይቻለናል። ያኔ በመጥፎ ነገር የተሳቀቀው ልባችንና አእምሮአችን በደስታና በተስፋ በሳቅና በፍቅር ይሞላል። ይህ... ነው Posititve thinking  እና Emotional Intelligence  እየተባለ የሚነገረው። ሀዘን ሀዘንን፣ ክስ ክስን፣ ወቀሳ ወቀሳን ይወልዳሉ መጥፎነታቸው ደግሞ እንደ ተላላፊ መሆናቸው ነው። ዐየሩ በዚህ ከተሞላ ሁሉም ይታመማል። ...."* በማለት የጻፉትን ለኔ እንደተናገሩልኝ እቆጥረዋለሁ።

የአጼውን እና የእቴጌ ጣይቱን ይህን ጎደሎ ታሪካቸውን ጳውሎስ ኞኞ እንደጻፈው ተስፋዬ ነግሮናል። መላው አለምን ያስደነቀ፣ በቅኝ አገዛዝ ስር ይማቅቁ ለነበሩ የሶስተኛው አለም አገር ህዝቦች ምሳሌ የሆነ፣ የአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለሞችን ቦታ እና ቅርጹን በመለዋወጥ የአብዛኛው ቅኝ ተገዥ አገር ህዝቦች እንደተስቦ እስኪቀባበሉት ድረስ...  ከጎላ ታላቅ ስራቸው ጋር ጽፎታል። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የአፍሪካ እና ላቲን አሜሪካ አገሮች ባንዲራቸው፣ ቅርጹና ቦታው ቢለያይም፣ ሶስቱን ቀለማት የያዘ የመሆኑ ምክንያት፣ የኢትዮጵያን የነጻነት ታሪክ፣ በተለይም ከአድዋው የሚኒሊክ ታሪክ ጋር ቁርኝት እንዳለው ካሁን ቀደም ማንበቤን አስታውሳለሁ። ይህን እውነታ የግንቦት ሰባቱ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌም ባንድ ቃለ-ምልልስ ወቅት ሲናገሩ ሰምቻለሁ። እዚህም ጥሩ መረጃ አለ።

ተስፋዬ በዚሁ ጽሁፉ፣ በሚኒሊክ እና አልጣሽ ምልልስ ውስጥ፣ የፈጠራ ችሎታውን በገንቢ መልኩ ተጠቅሞበትም አሳይቶናል፡--

> አልጣሽ፡ "ጣይቱስ እንዴት ናት?"
> ሚኒሊክ፡ "አጋዤ ናት..."

አልጣሽ፡ "ልጅ ባለመውለዷ ይሰማት ይሆን?"
ሚኒሊክ፡ "ጣይቱ ብርቱ ናት። *ስለልጅ ሳነሳባት 14 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ልጃችን ነው* ትላለች። አምላክ ልጅ ከለከላት…"

በነካካ እጅህ ይህን አይነት ገንቢ የሆነ የፈጠራ ስራህን በመጠቀም፣ ስለ ሃገር አንድነት እና ስለ ቀደምት መሪዎቻችን ለህዝብ ቅን አሳቢነትም ብዙ ጻፍልን። የሚኒሊክ፣ የጣይቱ፣ የቴዎድሮስን… መጥፎነት፣ የሃገሪቱን አንድነት የመናዱን ስራ እንደሆነ የመለስ አገዛዝ 'የታሪክ ጸሃፊዎች' እንቅልፍ እስኪያጡ በርትተው እየሰሩበት ነው። እንዲህ መሰል አፍራሽ ይዘት ያላቸውን መጽሃፍት የትምህርት ማጣቀሻ እስከማድረግ ደርሰዋል።

ይህ የእቴጌ ጣይቱ "… 14 ሚሊየን የኢትዮጵያ ህዝብ ልጃችን ነው.." አባባል ያስታወሰኝ ቢኖር ቦሌ ጎዳና ላይ የወደቁት ፣ ያሁኒቱን ቀዳማይ እመቤታችንን ልጆች ነው። ከጥቂት አመታት በፊት ከአንዱ የመለስ አገዛዝ *ልሟታዊ ጋዜጠኛ* ጋር ባደረገችው ቃለ-ምልልስ፤ ቀዳማይ እመቤት አዜብ እና ቤተሰቧ የመጨረሻ ድሃ መሆናቸውን እና እንዲያውም ገንዘብ እንደማትይዝ፣ ብትይዝም እንኳን ቦሌ መንገድ ዳር ለወደቁ ፣ የጎዳና ልጆች (ልጆቿም ናቸው) እንደምታድል የተናገረችውን እዚህ ያዳምጡ። ያንድ አገር ቀዳማይ እመቤት፣ እንዲህ *ትንሽ* ታስባለች ብሎ ማን ያስባል? እመቤታችን ጉደኛ ናት።… ከጋብቻ ውጭ "ተደራቢ" ወንድ (*"ውሽማ" ብሎ መጥራት ነውር ሆኖባት ነው)* መያዝ "… ለሴቶች የተቀመጠ ጥሩ መብት ነው። ሴቷም መስረቅ ትችላለች ማለት ነው" የምትል፣ ስለሴቶች መብት እንዲህ የጠለቅ እውቀት ያላት ቀዳማይ እመቤት ማግኘት *መታደል* ነው።

ቸር ይግጠመን!